ለታሪኮ_የፍቃድ መቀበያ ቅፅ

*እባክዎ በሚገባ አንብበው ፊርማዎትን ያስቀምጡ*

➢ **እኛ ማን ነን**



ኤምኤስኤፍ አለማቀፍ ገለልተኛ የሰብዓዊ ህክምና እርዳታ የሚሰጥ ተቋም ነው። በገጬት፣ በወረርሺኞች በአደጋዎች ወይም የህክምና አገልግሎት ባለማግኘት ለተጎዱ የህክምና አገልግሎት እንሰጣለን። የህክምና ዕርዳታ ይሰጣል። ስራችን አለም አቀፉ የህክምና ስነምግባርን መሰረት ያደረገ ሲሆን፣ገለልተኝነት፣ያላማዳላት መርሆችን ያክብራል፣

➢ **ለምን**

ምስል እና ታሪኮችን በመጠቀም ለሰዎች ህይወት ምን እንደሚመስል እና እኛ በተለያዩ ቦታዎች ምን እንደምንሰራ እንገልፃለን። ይህም ሰዎች ገቢ በማሰባሰብ እንዲደግፉንና፤ ለታካሚዎቻችን እና በምንሰራበት ማህበረሰብ ለምናደርገው ዘመቻ በመተባበር ድጋፍ እንዲሰጡን ያበረታታቸዋል።

➢ **ምን**



ታሪክዎን በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምፅ እና በተንቀሳቃሽ ምስል በመቅረጽ እናስቀምጣለን። ለዚህ ክፍያ አንስጥም ንብረትነቱም የኛ ነው። ታሪክዎ ውስጥ የግሎ የሆነና ለሌላ ሰው እንዲተላለፍ የማይፈለጉት መረጃ ይኖራል። ይህም ሲሆን ለምሳሌ ስምዎን፣ እድሜዎን እና አድራሻዎን እንዳይጠቀስ ፍቃደኝነትዎን አለመሰጠት ይችላሉ።

➢ **የት**



ታሪክዎ የእርሶን ሀገር ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች ሊሰራጬ ይችላል። ታሪክዎ በሌላ ቋንቋም ተተርጉሞ ሊቀርብ ይችላል። ታሪክዎን ፣ምስሎን እና ተንቀሳቃሽ ምስሎን በበይነመረብ ፣በጋዜጣ፣ በገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች እና በህትመት ሚዲያ በአለም ዙሪያ ሊታዩና ሊሰሙ ይችላሉ።



➢ **እንዴት**

የኛን እርዳታ ለሚፈልጉ ለመድረስ ከመንግስት፣ ከሚዲያ፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከአጠቃላዪ ማህበረሰብ ጋር አብረን እንስራለን። እነዚህ አጋሮቻችን ታሪክዎን የእኛን ስራ፣ ከእኛ ጋር የሚሰሩትን ወይም በስራው ዙሪያ ያሉ ነገሮችን ለማስተዋወቅ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ሊያሳትሟቸው እና ለራሳቸው ግንኙነት ሊጠቀሙባቸውም ይችላሉ።

➢ **መቼ**



ፍቶ ከተነሱ ፍቶ አንሺው ወይም ኤም ኤስ ኤፍ ፎቶዎን ለአምስት አመት በየትኛውም የአለም ክፍል በበይነመረብ ፣ በቴሌቪዥን እና በጋዜጣ በማሳተም ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የፎቶ አንሺው ከዚህ ላለፈ ነገር ሊጠቀምበት ቢፈልግ የኤምኤስኤፍን ፍቃድ ማግኘት አለበት።ኤምኤስኤፍ የእርሶን ፍላጎት ከግምት ውስጥ ስለሚያስገባ ለንግድ ፍቶዎን አይጠቀምም። ታሪኮን ካካፈሉን ከአምስት በኋላ ኤምኤስኤፍ በጥንቃቄ ያስቀምጠዋል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በልዩ ሁኔታዎች ብቻ ይጠቀማባቸዋል። ለምሳሌ በአመታዊ በዓላትና ወደ ኋላ ለመመለስ ሲያስፈልግ ሊጠቀምባቸው እንችላለን። ምስሎን እና ታሪኮን ከአምስት አመት በላይ እንድንጠቀም ከፈቀዱ ከታች ባለው ቅፅ ላይ ምልክት ያድርጉ።

**ሐሳቦን ከቀየሩ**

ሐሳቦን ለወደፊቱ ሊቀይሩ እነደሚችሉ እንረዳለን። ይህ ከሆነ በአስፈለገዎ ግዜ ለእኛ ማሳወቅ ይችላሉ። ታሪኮ እንዲነገር ካልፈለጉ ፣ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ካሎት

- ➢ በ tdataprotection.IO@geneva.msf.org መልዕክት በመላክ
- ➢ በአካባቢዎ በሚገኝ የኤምኤስኤፍ ቢሮ

ሀሳብዎን መቀየርዎን እንዳሳወቁን ታሪኮን ከፈይላችን በማጥፋት መጠቀማችንን እናቆማለን። የፋይል ክምችታችን ውስጥ ገብተው ታሪኮን ማስተካከል / ማሻሻል ይችላሉ።

የእርሶን ወይም የልጅዎን ታሪክ እና ምስል ኤምኤስኤፍ እዲቀርፅ በመፍቀድዎ እናመሰግናለን። ምስሎችን እንዴት ልንጠቀም እንደምንችል የሚያሳዩ ምሳሌዎች።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ሚስጥራዊ/ስሜታዊ መረጃ ማለት ምን ማለት ነው?**

ታሪኮዎ የግል ጉዳይዎን የተመለከቱ /የእርሶን የፖለቲካ አቅዋም፣ብሔር፣ ሀይማኖት፣የንግድ ማህበር አባልነት፣የጤና ሁኔታ፣ የፍቅር ግንኙነት ህይወት ወይም የወንጀል ታሪኮ ወይም የጀርባ ታሪኮችን ካካተተ ሌሎች የግል / ሚስጥራዊ የምንላቸው መረጃዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሳሌ የግል ወይም ማስታወስ የማይፈልጉትና ስነልቦናዊ ተፅዓኖን ያሳደረቦት ነገር ወይም ቤተሰቦት ላይ የተሰተን መረጃ ያካትታል።

**ታሪኬን እንዴት ልትጠቀሙበት እንዳስባችሁ ብታስረዱኝ**

ታሪኮን ለሚከተሉት ልናካፍል እንችላለን

_ ከእኛ ጋር የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ እና ሌላ ተቋማት

__ ስራችንን በገንዘብ እና በሌላ መንገዶች ድጋፍ ለሚሰጡን ተቋማት፣ ድርጅቶች እና ግለሰቦች

_ የእኛን ስራ ለሚዘግቡ የሚዲያ ተቋማት ፥ ለቴሌቪዥን ፣ ጋዜጣ፣ መፅሔት እና ሬድዮ አስተላላፊዎች

_ፎቶ አንሺዎች፣ፊልም ሰሪዎች እና እነሱን የሚወክሏቸው ተቋማት

**እንዴት ሚስጥራዊ ሊደረጉ ይችላሉ።**

ከእርሶ የሚገኘው መረጃ በጥንቃቄ በዲጅታል መዝገብ ቤታችን ተቀምጦ በኤምኤስኤፍ አለማቀፍ ቢሮ ሃላፊነት ይቀመጣል። የሚሰጡንን መረጃ በሚገባ በመመዝገብ በጥንቃቄ እናስቀምጣለን።

**አምስት አመት ካለፈ በኍላ ታሪኮን መቼ እንጠቀመዋለን?**

_የኤምኤስኤፍን ታሪክ ስናስታውስ

_በእርሶ ላይ በአምስት አመት ውስጥ ያለውን ለውጥ በማሳየት የኛን ስራ አስተዋፅኦ ለማሳየት

በአስተርጓሚ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ከመፈረሞ በፊት አስተርጓሚው በቅጹ ላይ የሰፈሩትን አንብቦ መረዳትዎን ማረጋገጥ አለበት።

**በአስተርጓሚወው የሚሞላ**

ያስረዳበት ቋንቋ፡ ቀን : ______

የአስተርጓሚው ስም፡

የባለታሪኩ ሙሉ ስም(አዋቂ/ አሳዳጊ )
እድሜ
የባለታሪኩ ሙሉስም ( ህፃን / ታዳጊ)
እድሜ
ስልክ/ ኢሜል/ አድራሻ

ታሪኬን ኤምኤስኤፍ እንዲጠቀም ፍቃዴን ሰጥቻለሁ። ታሪኬም የግሌ እና ሚስጥራዊ እንደሆነ አውቃለሁ።

የባለታሪኩ/ የአዋቂ ፊርማ
ቀን
የህፃኑ /ታዳጊው ፊርማ ( የግድ አይደለም)
ቀን

☐ እኔ የታዳጊው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ነኝ ለታዳጊውም ፍቃድ የመስጠት ስልጣን አለኝ

☐ የእኔ ወይም የልጅ ታሪክ ከ5 አመት በላይ እንዲጠቀሙ

ለታሪኮ_የፍቃድ መቀበያ ቅፅ

ታሪኮ ወይም ፎቶዎን ያነሳው የተመዘገበው (ወይም የልጅ ታሪኮ /ፎቶ) ________________
ጥያቄ ካልዎት ወይም ሀሳብዎን ከቀየሩ በአቅረቢያዎ ያለው የኤምኤስኤፍ ቢሮ በመቅረብ:___________

ወይም በኢሜል;
dataprotection.I0@geneva.org --------------------

ታሪኮዎን እንዴት እንደምንመዘገብ እና እንደምንጠቀም ለበለጠ መረጃ እባኮዎ የሚስጥር ፖሊሲ በድህረገፃችን በመግባት ያንብቡ
https://www.msf.org/privacy-policy

የኤምኤስኤፍ መረጃ ሰብሳቢ (የኤምኤስኤፍን ሰራተኛ/ ኮንትራክተር)

ሁሉም መረጃ ሰብሳቢዎች ፊርማ ከማግኘታቸው በፊት የኤምኤስኤፍን አዲዬ የቪዥዋል መመሪያ ማንበብ አለባቸው።

☐ መመሪያውን አንብቤ ተረድቻለሁ መመሪያውን እንደምከተል አረጋግጣለሁ።

☐ ታሪኩ ለባለታሪኩ ድጋሚ ተነበ ፍቃድ በድጋሚ ተገኝቷል (ግዴታ አይደለም)

እባክዎ **የፍቃድ ቅፅን** አንድ ኮፒ ለባለታሪኩ ይስጡ።

| የመረጃ ሰብሳቢው ስም | ቀን | ቦታ | የፕሮጀክት ሪፍረንስ |
|---|---|---|---|
| | | | |